# የያዕቆብ ወንድም የይሁዳ መልእክት

1 የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና የያዕ
ቆብ ወንድም ይሁዳ፤
ለተጠሩት፣ በእግዚአብሔር አብ ለተወ
ደዱትና በኢየሱስ ክርስቶስ ለተጠበቁት[ሀ]፤
[2]ምሕረት፣ ሰላምና ፍቅር ይብዛላችሁ።

## የዐመፀኞች ኀጢአትና የሚጠብቃቸው ፍርድ

[3]ወዳጆች ሆይ፤ አብረን ስለምንካፈለው
ድነት ልጽፍላችሁ እጅግ ጓጕቼ ነበር፤
ነገር ግን ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ ስለ
ተሰጠው እምነት እንድትጋደሉ ለመምከር
እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ። [4]ከረጅም
ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ[ለ] የተጻፉ አንዳንድ
ሰዎች ሾልከው ወደ እናንተ ገብተዋልና፤
እነርሱ ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌላቸው፣ የአም
ላካችንን ጸጋ በርኵሰት የሚለውጡና እርሱ
ብቻ ልዑል ገዥችንና ጌታችን የሆነውን
ኢየሱስ ክርስቶስን የሚክዱ ናቸው።
[5]ምንም እንኳ አስቀድማችሁ ይህን ሁሉ
የምታውቁ ቢሆንም፣ ጌታ[ሐ] ሕዝቡን ከግ
ብፅ ምድር እንዴት እንዳወጣ፣ በኋላ ግን
ያላመኑትን እንዳጠፋ ላስታውሳችሁ እወዳ
ለሁ። [6]የሥልጣን ስፍራቸውን ያልጠበቁ
ትን ነገር ግን መኖሪያቸውን የተዉትን
መላእክት በዘላለም እስራት እስከ ታላቁ
ቀን ፍርድ ድረስ በጨለማ ጠብቆአቸ
ዋል። [7]እንዲሁም ሰዶምና ገሞራ፣ በዙሪያ
ቸውም ያሉ ከተሞች ለሴሰኛነትና ከተፈጥሮ
ሥርዐት ውጭ ለሆነ ሩካቤ ሥጋ ራሳቸውን
አሳልፈው ሰጡ፤ እነርሱም በዘላለም እሳት
በመቀጣት ለሚሠቃዩት ምሳሌ ሆነዋል።
[8]በዚህ ሁኔታ እነዚህ ሕልም አላሚዎች
የገዛ ሥጋቸውን ያረክሳሉ፤ ሥልጣንን ይቃ
ወማሉ፤ በሰማይ ክብር ያላቸውንም ፍጥረታት
ይሳደባሉ። [9]የመላእክት አለቃ የሆነው ሚካ
ኤል እንኳ ስለ ሙሴ ሥጋ ከዲያብሎስ ጋር
በተከራከረ ጊዜ፣ "ጌታ ይገሥጽህ" አለው
እንጂ የስድብ ቃል በመናገር ሊከሰው
አልደፈረም። [10]እነዚህ ሰዎች ግን የማያወቁትን
ነገር ሁሉ ይሳደባሉ፤ አእምሮ እንደሌላቸው
እንስሳት በደመ ነፍስ በሚያወቁት ነገር
ይጠፋሉ።
[11]ወዮላቸው! በቃየን መንገድ ሄደዋል፤
ለገንዘብ ሲስገበገቡ በበለዓም ስሕተት
ውስጥ
ወድቀዋል፤ በቆሬም ዐመፅ ጠፍተዋል።
[12]እነዚህ ሰዎች በፍቅር ግብዣችሁ ላይ
ያለ አንዳች ኀፍረት ከእናንተ ጋር ቀርበው
የሚበሉ ነውረኞች ናቸው፤ ደግሞም ራሳ
ቸውን ብቻ የሚመግቡ እረኞች ናቸው፤
እነርሱም በነፋስ የሚነዱ ዝናብ የሌላቸው
ደመናዎች ናቸው፤ በመከር ወራት ፍሬ የ
ማይገኙባቸው ከሥራቸው ተነቅለው
ሁለት ጊዜ የሞቱ ዛፎች ናቸው። [13]የነውራ
ቸውን አረፋ የሚደፍቁ የተቈጡ የባሕር ማዕ
በል፣ ድቅ ድቅ ጨለማ ለዘላለም የሚጠ
ብቃቸው ተንከራታች ከዋክብት ናቸው።
[14]ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነው ሄኖክ
ስለ እነዚህ ሰዎች እንዲህ ሲል ተንብዮአል፤
"እነሆ፤ ጌታ ከእልፍ አእላፋት ቅዱሳኑ ጋር
ይመጣል፤ [15]ይህም፣ በሰው ሁሉ ላይ ለመ
ፍረድ እንዲሁም ዐመፀኞችን ሁሉ በክ
ፋት መንገድ በሠሩት የዐመፅ ሥራና
በክፋት በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩት የስድብ
ቃል ሁሉ አጥፊነታቸውን ይፋ ለማድረግ
ነው"። [16]እነዚህ ሰዎች የሚያጕረመርሙና
ሌሎችን ሰዎች የሚከሱ ናቸው፤ ርኩስ
ምኞታቸውን ይከተላሉ፤ በራሳቸው ይታበ
ያሉ፤ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ሌሎችን ይክ
ባሉ።

## ጸንቶ ስለ መቆም የቀረበ ጥሪ

[17]ነገር ግን ወዳጆች ሆይ፤ የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት አስቀድመው
የተናገሩትን አስታውሱ። [18]እነርሱም፣ "በመ
ጨረሻው ዘመን ርኩስ ምኞታቸውን የሚከ
ተሉ ዘባቾች ይመጣሉ" ብለዋችኋል። [19]እነ
ዚህ ሰዎች በመካከላችሁ መለያየትን የሚፈ
ጥሩ፣ በደመ ነፍስ የሚነዱ መንፈስ የሌላ
ቸው ናቸው።
[20]እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፤ እጅግ ቅዱስ
በሆነው እምነታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ
ትጉ፤ በመንፈስ ቅዱስም ጸልዩ። [21]ወደ ዘላ
ለም ሕይወት የሚያደርሳችሁን የጌታችንን
የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ
ሳለ፣ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን
ጠብቁ።
[22]ተጠራጣሪ ለሆኑት ራሩላቸው፤ [23]አን
ዳንዶችን ከእሳት ነጥቃችሁ አድኗ
ቸው፤ ለሌሎች ደግሞ በርኩስ ሥጋ የተ
በከለውን ልብሳቸውን እንኳ እየጠላችሁ
በፍርሀት ምሕረት አሳዩአቸው።

## ቃለ ውዳሴ

[24]እንዳትወድቁ ሊጠብቃችሁና ያለ
ነቀፋና በደስታ በክብሩ ፊት ሊ
ያቀርባችሁ

1፥1 ማቴ13፥55፤
ዮሐ14፥22፤17፥12፤
ሐሥ1፥13፤ሮሜ1፥1፤6፥7
1፥2 ሮሜ1፥7፤
ገላ 6፥16፤1ጢሞ1፥2
1፥3 ቀኁ20፤
ሐሥ 6፥7፤9፥13፤
1ቆሮ 10፥14፤
1ጢሞ6፥12፤ቲቶ1፥4
1፥4 ገላ2፥4፤
ቲቶ1፥16፤2ጴጥ2፥1፤
1ዮሐ2፥22
1፥5 ዘኁ14፥29፤
ዘዳ 1፥32፤2፥15፤
መዝ 106፥26፤
1ቆሮ10፥1-5፤ዕብ3፥16፡
17፤2ጴጥ1፥12፡13፤3፥1፡
2፤ 1ዮሐ2፥20
1፥6 2ጴጥ2፥4፡9
1፥7 ዘዳ29፥23፤
ማቴ10፥15፤25፥41፤
2ጴጥ3፥7
1፥8 2ጴጥ2፥10
1፥9 ዘዳ34፥6፤
ዳን10፥13፡21፤12፥1፤
ዘካ3፥2፤1ተሰ4፥16፤
ራእ12፥7
1፥10 2ጴጥ2፥12
1፥11 ዘፍ4፥3-8፤
ዘኁ16፥1-3፡31-35፤
ዕብ11፥4፤2ጴጥ2፥15፤
1ዮሐ3፥12
1፥12 ምሳ25፥14፤
ሕዝ34፥2፡8፡10፤
ማቴ15፥13፤
1ቆሮ11፥20-22፤
ኤፌ4፥14፤
2ጴጥ2፥13፡17
1፥13 ኢሳ57፥20፤
ፊል3፥19፤2ጴጥ2፥17
1፥14 ዘፍ5፥18፡
21-24፤ዘዳ33፥2፤
ዳን7፥10፤ ዘካ14፥5፤
ማቴ16፥27፤ዕብ12፥22
1፥15 1ጢሞ1፥9፤
2ጴጥ2፥6-9
1፥16 ቀኁ18፤1ቆሮ
10፥10፤2ጴጥ2፥10፡18
1፥17 ኤፌ4፥11፤
ዕብ2፥3፤2ጴጥ3፥2
1፥18 ቀኁ16፤
1ጢሞ 4፥1፤
2ጢሞ3፥1፤
2ጴጥ2፥1፤3፥3
1፥19 1ቆሮ2፥14፡15
1፥20 ቀኁ3፤ኤፌ6፥18፤
ቈላ2፥7፤1ተሰ5፥11
1፥21 ማቴ25፥46፤
ቲቶ2፥13፤ዕብ9፥28፤
2ጴጥ3፥12
1፥23 አሞ4፥11፤
ዘካ 3፥2-፤1ቆሮ3፥15፤
ራእ3፥4
1፥24 ሮሜ16፥25፤
2ቆሮ4፥14፤ቈላ1፥22

[ሀ]1 ወይም *የተጠበቁት* ሊሆን ይችላል
[ለ]4 ወይም *ፍርድ የተወሰነባቸውን ሰዎች*
[ሐ]5 አንዳንድ የጥንት ቅጆች *ኢየሱስ* ይላሉ

ለሚችለው፣ 25እርሱ ብቻ አዳኛችን ለሆነው
አምላክ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል

1÷25 ዮሐ5÷44፤
ሮሜ11÷36፤
1ጢሞ 1÷17፤
ዕብ13÷8

ከዘመናት ሁሉ በፊት፣ አሁንና እስከ
ዘላለምም ድረስ ክብር፣ ግርማ፣ ኀይልና
ሥልጣን ይሁን፤ አሜን።